# የአቅጣጫ እና የደህንነት ኮርስ መግቢያ

የፓስፊክ ሾር ትምህርት ቤት

- እንኳን በደህና መጡ፣ ወደ ፓሲፊክ ሾር ማሰልጠኛ ማእከል። ይህ አቅጣጫ እና ደህንነት ትምህርት መግቢያ ነው። ወደ ትምህርቱ ከመግባታችን በፊት፣ በዚህ ኮርስ ምን እንደሚጠብቁ አጠር ያለ መግለጫ ልሰጥዎ እፈልጋለሁ።

- የአቅጣጫ እና የደህንነት ክፍል፣ በማህበራዊ እና ጤና አገልግሎቶች ዲፓርትመንት (DSHS) ፣የጸደቀ የ5 ሰአታት የስልጠና ፕሮግራም ነው። እና ለሁሉም የረጅም ጊዜ እንክብካቤ ሰራተኞች፣ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት መውሰድ ግዴታ ያለባቸው ክፍል ነው።
- ይህ አስፈላጊ ስልጠና፣ ተንከባካቢዎችን ደህንነቱ የተጠበቀ፣ እና ውጤታማ እንክብካቤን ለመስጠት፣ እውቀትን እና ክህሎቶችን ያስታጥቃቸዋል።

- ትምህርቱ በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ነው።
  - የአቅጣጫ ኮርስ፡ 2 ሰአታት ይወስዳል፣ እና ስለ ተንከባካቢ፣ ሚና፣ ሀላፊነቶች እና የደንበኛ መብቶች፣ እና እንዲሁም የግንኙነት አስፈላጊ ነገሮችን መግቢያ ይሸፍናል።
  - የደህንነት ኮርስ፡ 3 ሰአታት ይወስዳል፣ እና ጉዳትን ለመከላከል፣ አደጋዎችን በመለየት እና በማስተዳደር ላይ፣ የአደጋ ጊዜ ምላሽ እና በኢንፌክሽን ቁጥጥር ላይ ያተኩራል።

- የኦሬንቴሽን ወይም አቅጣጫ ኮርስ፣ በመጀመሪያ የሚወሰድ ትምህርት ነው።
- አዲስ ሰራተኞችን ወይም ግለሰቦችን ከአዲሱ የስራ ቦታ ባህል፣ የደህንነት ፖሊሲዎች እና የስራ ተስፋዎች ጋር ለማስተዋወቅ የተነደፈ ነው።
- አዲስ ሰራተኞችን ወደ  ደንበኞን መንከባከብ ሥራ ሲገቡ፣ በቀላሉ  መሰረታዊ እውቀት እንዲያገኙ  ያደርጋል።

- የኦሬንቴሽን እና ደህንነት ኮርስ ክፍል አላማ፣ አዳዲስ ሰራተኞች ሚናቸውን፣ እና ሃላፊነታቸውን እንዲገነዘቡ፣ የደህንነት ደንቦችን እንዲያውቁ፣ እራሳቸውን እና ሌሎችን በሚጠብቅ መልኩ፣ ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው።

- ደህንነት ሲባል ሰራተኞች እራሳቸውን፣ የስራ ባልደረቦቻቸውን እና ደንበኞቻቸውን በሚሰሩበት ጊዜ፣ ከሚደርስባቸው ጉዳት፣ ለመከላከል ሊረዱቸው የሚገቡትን አስፈላጊ እውቀት እና ተግባራት የሚያመለክት ነው።
- የደህንነት ደንቦችን በመከተል፣ አደጋዎችን በመከላከል እና ለድንገተኛ አደጋዎች ውጤታማ ምላሽ በመስጠት፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የስራ አካባቢ መፍጠር ላይ ያተኩራል።

- በአቅጣጫ እና በደህንነት ኮርስ ውስጥ ያለው የደህንነት ትምህርት ዓላማ፣ ሁሉም ሰራተኞች አደጋዎችን እና ጉዳቶችን ለመከላከል፣ ድንገተኛ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር፣ የጤና እና የደህንነት ፕሮቶኮሎችን በመከተል፣ በዋሽንግተን ስቴት ህጎች መሰረት፣ እውቀት እና ክህሎት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ ነው።

- የአቅጣጫ እና የደህንነት ስልጠና፣ ተማሪዎች አዲሱን አካባቢ በአስተማማኝ እና በብቃት ለመምራት፣ አስፈላጊውን እውቀት እና ክህሎት እንዲኖራቸው ይረዳል። ይህን ኮርስ ሲጨርሱ፣ በአስተማማኝ ሁኔታ ለመስራት፣ ለአደጋ ጊዜ፣ በልበ ሙሉነት እና በጥንቃቄ፣ ምላሽ ለመስጠት እና ለራሳቸው፣ ለስራ ባልደረቦቻቸው እና ለሚያገለግሉት ደንበኞች፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ የስራ አካባቢን ለመጠበቅ፣ ባለው ችሎታዎ ላይ በራስ የመተማመን ስሜት ይሞላሉ።

# ሞጁል 1፤የደንበኛ መብቶች እና ደንበኞች የሚኖሩበት ቦታ

- ትምህርት 1፤ የደንበኞችን መብቶችን መረዳት
- ትምህርት 2፤ ደንበኞች የሚኖሩባቸው ቦታዎች

# ሞጁል 2፤ የLTC ሰራተኞች መሰረታዊ ሀላፊነቶች

- ትምህርት 1፤ የእንክብካቤ እቅዱን መረዳት
- ትምህርት 2፤ ተግባራትን በትክክል ያከናውኑ
- ትምህርት 3፤ መመዝገብ እና ለውጦችን ሪፖርት ማድረግ
- ትምህርት 4:፤ በድንገተኛ ሁኔታዎች ውስጥ ተገቢውን ነገር ያድርጉ
- ትምህርት 5፤ ፕሮፌሽናል ሁን
- ትምህርት 6፤ የሥራ መልቀቅያ ግዜ

# ሞጁል 3፤ በደንበኛ እንክብካቤ ውስጥ ፕሮፌሽናል መሆን

- ትምህርት 1፤ የመጀመሪያ ቀን እይታዎች
- ትምህርት 2፤ ማዳመጥ
- ትምህርት 3፤ የሰውነት ቋንቋ
- ትምህርት 4፤ እንደገና ጠይቅ

# ሞጁል 4፤ በሥራ ቦታ ውጤታማ ግንኙነት

- ትምህርት 1፤ ከተቆጣጣሪዎ ጋር ውጤታማ ግንኙነት
- ትምህርት 2፤ ከእንክብካቤ ቡድን አባላት ጋር መግባባት
- ትምህርት 3፤ የስልክ ሥነ ምግባር
- ትምህርት 4፤ የአደጋ ጊዜ ፕሮቶኮሎች ማወቅ

# ሞጁል 5፤ መከታተል፣ መጠበቅ እና ሪፖርት ማድረግ

- ትምህርት 1፤ ምልከታ፣ ሰነድ መስጠት እና ምላሽ መስጠት
- ትምህርት 2፤ የደንበኛ ደህንነት፣ ጥበቃ እና መብቶች
- ትምህርት 3፤ ህጋዊ እና ሥነ ምግባራዊ ኃላፊነቶች

# ሞጁል 6፤በእራስዎ እና በደንበኞች ላይ ጉዳቶችን ይከላከሉ

ትምህርት 1፤በተገቢው የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ጀርባዎን ያጠናክሩ እና ይጠብቁ

ትምህርት 2፤ ተገቢውን የማንሳት ቴክኒኮችን መጠቀም እና ጉዳቶችን ለመከላከል ሽፍን ጫማ ማድረግ

ትምህርት 3 ፤ መውደቅን መከላከል እና ደህንነት መጠበቅ

# ሞጁል 7፤ በእራስዎ እና በደንበኞች ላይ አደጋዎችን ይከላከሉ

ትምህርት 1፤ አደጋዎችን መከላከል እና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን መጠበቅ

ትምህርት 2፤ የስራ ቦታ ደህንነት፣ እና አደጋ መከላከል

ትምህርት 3፤ የስራ ቦታ ደህንነት

# ሞጁል 8፤የኢንፌክሽን ቁጥጥር እና የደህንነት ልምዶች

- ትምህርት 1፤ መደበኛ የኢንፌክሽን ቁጥጥር
- ትምህርት 2፤ ለደም ወለድ በሽታ መጋለጥን መከላከል
- ትምህርት 3፤ በቤት ውስጥ የተበከሉ ቁሳቁሶችን በአስተማማኝ ሁኔታ መቆጣጠር

# ሞጁል 9፤የደህንነት እና የጤና አካባቢን መጠበቅ

- ትምህርት 1፤ ውጤታማ ጽዳት እና ፀረ-ተባይ ልምምድ
- ትምህርት 2፤ የቤት ውስጥ ኬሚካሎችን ደህንነቱ የተጠበቀ አያያዝ
- ትምህርት 3፤ ሌላውን ለመጠበቅ ሲታመሙ ቤት ይቆዩ

# ሞጁል 10፤ ለአደጋ ጊዜ ዝግጅት እና እውቀት

- ትምህርት 1፤ አጠቃላይ የአደጋ ጊዜ እቅድ ማውጣት
- ትምህርት 2፤ የደንበኛ-የአደጋ ጊዜ እቅድን መረዳት
- ትምህርት 3፤ በአደጋ ጊዜ መልቀቂያ መንገዶች ጋር መተዋወቅ።
- ትምህርት 4፤ የቅድሚያ መመሪያ እና ፖስት ፎርሞችን (POLST forms) በድንገተኛ ጊዜ ማስተዳደር

# ሞዱል 11፤ በአደጋ ጊዜ ምላሽ እና ልምምድ

ትምህርት 1፤ የአደጋ ጊዜ መልቀቂያዎችን መለማመድ
ትምህርት 2፤ ለተፈጥሮ አደጋዎች እና ድንገተኛ አደጋዎች ምላሽ መስጠት
ትምህርት 3፤ ተረጋግቶ መኖር እና በራስ በመተማመን መምራት

- በፓሲፊክ ሾር ማሰልጠኛ ማእከል የሚሰጠው የአቅጣጫ እና ደህንነት ስልጠና ኮርስ ሲመችዎት እና ሲመቻችሎት እንዲወስድት የተዘጋጀ ነው።
- ተንከባካቢዎች በማንኛውም ጊዜ፣ ክፍሉን ለአፍታ ማቆም እና ዝግጁ ሲሆኑ በማንኛውም ጊዜ መቀጠል ይችላሉ፣ ይህም በራስ የመመራት ሂደት እንዲኖር ያስችላል።

- እያንዳንዱ ሞጁል፣ ለተማሪዎች በእንክብካቤ ሥራቸው ላይ ጠቃሚ ትምህርቶችን በማቅረብ ፣ በቀላሉ ሊታተሙ የሚችሉ ማስታወሻዎችን ያካትታል።
- ይህም ተንከባካቢዎች በተግባራቸው ውስጥ ጠንካራ መሰረት እንዲኖራቸው ያደርጋል።

- ትምህርቱ መማርን ለማጠናከር ብዙ ጥያቄዎችን ያካትታል።
- ተማሪዎች ሁሉንም ጥያቄዎች በአቅጣጫ እና ደህንነት ማሰልጠኛ ኮርስ ቢያንስ 80 በመቶ ማለፍ ይጠበቅባቸዋል።
- ተማሪዎች የሚፈለገውን ነጥብ እስኪያገኙ ድረስ ትምህርቱን እንደገና ማንበብና መፈተን ይችላሉ። ፈተናውን ደጋግመው መውሰድ ይችላሉ፣ ምንም ገደብ የለውም።
- ይህ ሁሉም ተሳታፊዎች እንደ ተንከባካቢነት ሚናቸው በበቂ ሁኔታ መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣል።

- አቅጣጫ እና ደህንነት ስልጠና ኮርሱን በተሳካ ሁኔታ ሲያጠናቅቁ ተማሪዎች በ5 ሰአታት መርሃ ግብር መሳተፋቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ያገኛሉ።
- ይህ ሰርተፍኬት በማህበራዊ እና ጤና አገልግሎት ዲፓርትመንት (DSHS) የተቀመጡትን አስፈላጊ የሥልጠና ደረጃዎች እንዳሟሉ እና የረጅም ጊዜ የእንክብካቤ ሠራተኛ ሆነው ሥራቸውን ለመጀመር መዘጋጀታቸውን እንደ ማረጋገጫ ሆኖ ያገለግላል።

- የምስክር ወረቀትዎን በሚቀበሉበት ጊዜ፣ የሚከተሉትን ቁልፍ እውቀት እና ክህሎቶች አግኝተዋል።
  - አዲስ ሰራተኞች ሚናቸውን፣ ኃላፊነታቸውን እና የስራ ቦታን የደህንነት ደንቦች ይገነዘባሉ።
    - እና ደግሞ
  - አደጋዎችን ለመከላከል፣ ድንገተኛ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር እና የዋሽንግተን ስቴት የጤና እና የደህንነት ፕሮቶኮሎችን ለመከተል ሰራተኞችን እውቀት እና ክህሎት ማስታጠቅ።

አሁን የአቅጣጫ እና ደህንነት ክፍል አጠቃላይ እይታን አጠናቅቀዋል። እባክዎ ወደ ሞጁል 1 ይቀጥሉ።

# References


- https://media.pembinatrails.ca/docs/1f900dba-c0a6-4593-adc2-1afe08bb69b0_New Workers Banner - pic.jpg
- https://1streporting.com/wp-content/uploads/2022/08/image-37.jpeg
- https://www.accuform.com/files/damObject/Image/huge/LHTL303.jpg